# በጤና ሽፋንዎ ላይ ያሉ አስፈላጊ ለውጦች

ከጥቅምት 1፣ 2026 ጀምሮ አንዳንድ ዜጎች ያልሆኑ ሰዎች ለሜዲኬይድ የጤና ሽፋን ብቁ አይሆኑም። በኮንግረስ የፀደቀው እና በፕሬዚዳንት ትራምፕ የተፈረመው አዲሱ የፌዴራል ሕግ ሜዲኬይድን ማን ማግኘት እንደሚችል የሚቀይር ነው። ይህ ሕግ ተፈጻሚ የሚሆነው ዜጎች ባልሆኑ አዋቂ ሰዎች ላይ ነው፤ ነገር ግን በልጆች ወይም በነፍሰ ጡር ሰዎች ላይ አይተገበርም።

## መረጃዎቻችን እንደሚያሳዩት እነዚህ ለውጦች በቤትዎ ውስጥ ያለ ሰው ላይ ተጽፅኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

ከጥቅምት 1፣ 2026 ጀምሮ፣ ከእነዚህ ምድቦች ውስጥ በማንኛውም ዜጋ ካልሆኑ ለሜዲኬይድ ብቁ አይደሉም፡-

- ጥገኝነት የጠየቁ ሰዎች
- ስደተኞች
- ቢያንስ ለአንድ ዓመት በአሜሪካ ታስሮ የቆየ
- ከ1980 በፊት በቅድመ ሁኔታ መግቢያ የተፈቀደላቸው
- የተደበደቡ ዜጎች ያልሆኑ ሰዎች፣ የትዳር አጋሮች፣ ልጆች ወይም ወላጆች
- የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች እና የትዳር አጋር፣ ልጅ፣ ወንድም/እህት ወይም ወላጅ ወይም ለህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ ቪዛ ማመልከቻ አስገብተው በመጠባበቅ ላይ ያሉ
- ከአገር የመባረር እገዳ መብት የተፈቀደላቸው
- የአፍጋኒስታን እና የዩክሬን የጥበቃ ፕሮግራምን ጨምሮ የሰብአዊ መብት ጥገኝነት ጠያቂዎች

ይህ እርስዎን እንደሚመለከት እርግጠኛ ካልሆኑ ነፃ እርዳታ ከሜሪላንድ ሄልዝ ኮኔክሽን በ 1-855-642-8572 ማግኘት ይችላሉ። የደምበኛ ድጋፍ ክፍላችን ከ200 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች እንዲሁም መስማት ለተሳናቸው እና መስማት ለተቸገሩ ሰዎች የሚሆን መልዕክት ማስተላለፊያ አገልግሎት ይሰጣል።

እነዚህ ለውጦች በልጆች ወይም በነፍሰ ጡር ሴቶች ላይ ተጽዕኖ **አያሳርፉም**።

እነዚህ ለውጦች የጤናማ ሕፃናት ፕሮግራም ላይ ተጽዕኖ **አያሳርፉም**።

## ለእርስዎ የሚሆኑ ቀጣይ ሂደቶች

የሜዲኬይድ አባል ከሆኑ፣ አስፈላጊ አዳዲስ መረጃዎች እንዳያመልጥዎት አሁናዊ የአድራሻ መረጃዎን ያሳውቁ።

**የተለወጡ ነገሮች ካሉ ያሳውቁን።** የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ከተቀየረ ወይም ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ መረጃዎን በ MarylandHealthConnection.gov በኩል ያሳውቁ። ይግቡ እና "ለውጥ ያሳውቁ" የሚለውን ቁልፍ ይጠቀሙ።

**ሽፋንዎን አሁን ይጠቀሙ።** አሁንም ያለዎትን ሽፋን ለመጠቀም ከጥቅምት 1 በፊት ሐኪምዎን ይጎብኙ።

**የቤተሰብዎን አባላት ሽፋን ያስጠብቁ።** አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ለሽፋን ብቁ ባይሆኑም እንኳ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ሜዲኬይድ ሊያገኙ ይችላሉ።

- ➔ የዜግነት ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታን ማሳየት የሚያስፈልጋቸው የተወሰኑ ለሽፋን የሚያመለክቱ የቤተሰብ አባላት ብቻ ናቸው።
- ➔ ሰነድ የሌላቸው ወላጆች የአሜሪካ ዜጎች ለሆኑ ወይም ብቁ የሆነ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ላላቸው ልጆቻቸው ማመልከት አለባቸው።
- ➔ ለራስዎ ሽፋን እያመለከቱ ካልሆነ፣ የኢሚግሬሽን ሁኔታዎን ማቅረብ አያስፈልግዎትም።

የፌዴራል ለውጦች እርስዎ እና ቤተሰብዎ ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚኖረው የበለጠ ይወቁ።

## ተጨማሪ የጤና እንክብካቤ ግብዓቶች

**ሜዲኬይድዎ ካበቃ፣ አሁንም አማራጮች አለዎት።**

በካውንቲዎ ውስጥ ነፃ ወይም ተመጣጣኝ የጤና እንክብካቤ ለማግኘት፣ የእርስዎን የአከባቢ የጤና መምሪያ ይጎብኙ።

ለአእምሮ ጤና፣ ለባህሪ ጤና እና ለዕፅ አጠቃቀም አገልግሎቶች ከአካባቢዎ የባህሪ ጤና ባለስልጣን ጋር ይገናኙ።

ለገንዘብ ድጋፍ፣ ለድንገተኛ ሕክምና ወይም ለሌላ አስፈላጊ የሕክምና እንክብካቤ ከኪስዎ ሙሉ ወጪዎችን ለመክፈል አስቸጋሪ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ የሜሪላንድ ሆስፒታሎች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣሉ።

ለድንገተኛ አደጋዎች፣ እባክዎን 911 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ። ሆስፒታሉ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አስቸኳይ እንክብካቤ የሚያስፈልገውን የድንገተኛ ሕክምና ወጪ ሊሸፍን የሚችል የድንገተኛ ጊዜ ሜዲኬይድ ለማመልከት ሊረዳዎት ይችላል።

የማህበረሰብ ግብዓቶችን ለማግኘት፣ 2-1-1 ይደውሉ ወይም 211md.orgን ይጎብኙ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ ወደሚከተለው ድህረ-ገፅ ይሂዱ፦
marylandhealthconnection.gov/checkin